ቍ.2013-003 ፥ የካቲት ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ፡ (February| février 2021) ።
sh1@ttomar.net


| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "ዐድዋ ፥ የሥልጣኔ ፡ ላቂያ ፤ የሀገራዊነት ፡ ድል ። " |
| ደሁሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | የካቲት ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013-003 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |


# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتَاحي

# ዐድዋ ፥ የሥልጣኔ ፡ ላቂያ ፤ የሀገራዊነት ፡ ድል ።



አንድ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ዐምስተኛውን ፡ የዐድዋ ፡ ድል ፡ በዓል ፡ የካቲት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ እንሆ ፡ አክብረናል ፤ ለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

ኢትዮጵያ ፥ **የሥልጣን ፡ ተገቢነትን ፡** መርሕ ፡ በጥንታዊው ፡ የስያሳ ፡ (የ"ፖለቲካ") ፡ ሥርዐቷ ፡ በማስከበሯ ፥ የዐድዋ ፡ ጦርነትን ፡ ድል ፡ ተቀዳጅታለች ። በወቅቱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥቷ ፥ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ በትኽክለኛው ፡ ባለዐልጋ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ኾነው ፥ በስግብግብነት ፡ መንፈስ ፡ የመጣባቸውን ፤ ዘመናዊ ፡ መሣሪያን ፡ የታጠቀ ፤ ሥልጣኔ ፡ ግን ፡ የጐደለውን ፡ ጠላት ፡ ባንድነትና ፡ በፍጹም ፡ የመሥዋዕትነት ፡ ፈቃድ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ መቶው ፥ የሥልጣኔ ፡ ላቂያቸውን ፡ አረጋግጠዋል ።

ዛሬስ ፥ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሕዝባችን ፡ በምን ፡ ኹኔታ ፡ ይገኛሉ ፥ ጭቈና ፡ አጕብጧቸው ፤ ችጋር ፡ አክስቷቸው ፤ ጥርጣሬ ፡ አገንግኗቸው ፤ ሥጋት ፡ ውጧቸው ፤ ኀፍረት ፡ አጥልቋቸው ፤ ንዴት ፡ አብግኗቸው ፥ ጕስቍልናቸው ፥ እንኳን ፡ ለራሳችን ፥ ለባዕድም ፡ በግልጽ ፡ ይታያል ። *"ባለቤቱን ፡ ካልናቁ ፥ ዐጥሩን ፡ አይነቀንቁ"* ፡ ነውና ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሀገር ፡ ባለቤትነቱን ፤ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ አኹንም ፡ ባለማስከበሩ ፥ እንሆ ፡ ከመናቁ ፡ የተነሣ ፥ ማንም ፡ ዐይነ ፡ ደረቅ ፡ ከባዕድ ፡ ኀይል ፡ በኀቡዕ ፡ ተመሳጥሮ ፡ ጕልበትን ፡ እየገዛ ፡ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ በመውጣት ፥ ስለ ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዕጣ ፡ ፈንታ ፡ በስሚ ፡ ሊወስንና ፡ ሊዋዋል ፡ ቀንዳ ፡ ቀንዳ ፡ ይላል ። ከ*"ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ማሻሻል"* ፡ እስከ ፡ *"ክልል"* ፡ ማከፋፈል ፥ ከሀገራዊ ፡ ቋንቋ ፡ ምንዘራ ፡ እስከ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ቀየራ ፥ ከመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ሽያጭ ፡ እስከ ፡ ሀገር ፡ ዳር ፡ ድንበር ፡ ልዋጭ ፥ በጕዳዩ ፡ ኹሉ ፡ በማያገባው ፡ እየገባ ፡ የውንብድና ፡ እና ፡ የቅጥረኝነት ፡ ግብሩን ፡ አላንዳች ፡ ኀፍረት ፤ አላንዳች ፡ ሥጋት ፦ *"ምን ፡ እንዳታመጡ ፥ "* በሚል ፡ ትዕቢት ፥ ሲፈጽም ፡ እናየዋለን ። ይባስ ፡ ብሎ ፥ ነፍሳቸውን ፡ የሼጡ ፡ *"ፖለቲከኞች"* ፡ ደግሞ ፥ እንደ ፡ ዐምባ ፡ ገነኑ ፡ አለቃቸው ፡ ኹሉ ፥ እንግሊዝኛን ፡ በቀላቀለ ፡ ዘልባዳ ፡ አንደበታቸው ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፦ *"ሕዝቦች"* ፡ እያሉ ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ ህልውናውን ፡ ሲክዱበት ፡ እንሰማለን ።

*"ምርጫ"*ን ፡ ያራዘመው ፡ *"ኮሮና"* ፡ ተረስቶም ፥ ለስሙ ፡ *"የዐድዋ ፡ ድል ፡ በዓል"* ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ ይከበራል ፡ ተብለናል ፤ ዳሩ ፡ ግን ፥ ከቀደሙት ፡ 125 ፡ ዓመታት ፡ የባሰውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ህልውና ፡ ፈተና ፡ ውስጥ ፡ ገብቷል ። የምልክዮሽ ፡ ኀይሎችና ፡ ምንደኞቻቸው ፡ ከመቼውም ፡ ጊዜ ፡ የባሰ ፡ ዛሬ ፡ በሀገሪቱ ፡ መንግሥታውያን ፡ የሥልጣን ፡ ሕዋሳትና ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ በእየዘርፉ ፡ ሠርገው ፡ ገብተው ፥ ሀገራዊነት ፡ ላይ ፡ ያነጣጠረውን ፡ ስርጀታቸውንና ፡ ቅርምታቸውን ፤ ጭፍጨፋቸውንና ፡ ጥፋታቸውን ፡ በገሀድ ፡ ይፈጽማሉ ።

ይኹንና ፥ ዛሬ ፡ የሚታየው ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ የታጣበት ፤ ዐምባ ፡ ገነንነትና ፡ ቅጥረኝነት ፡ የሰፈነበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አሳዛኝ ፡ ስያሳዊ ፡ ኹኔታ ፥ ጊዜያዊ ፡ እንጂ ፡ ዘለቄታ ፡ አይኖረውም ። የዐድዋ ፡ ድል ፥ ጨለማውን ፡ ኹሉ ፡ ሠንጥቆ ፡ በሚፈነጥቀው ፡ ዘለዓለማዊ ፡ የተስፋና ፡ የድል ፡ አድራጊነት ፡ ብርሃኑ ፥ መጪውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ድኅነት ፡ በሚያዝያ ፡ 27 ፡ ድል ፡ አስቀድሞ ፡ አስተጋብቶ ፡ ዐውጇል ፤ ቸር ፡ ያሰማን ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ፡
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።